# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ጥቅምት 4 ቀን 2004 ዓ.ም.›**

**ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ እያቃታቸው መሆኑ ተጠቆመ፤**

**አባዱላ ገመዳ ከኦህዴድ ስራ አስፈጻሚነቱ ተነሳ፤**

**ቀጣይ ፕሬዝዳንት ሆኖ ይሾም ይሆን?**

**የወያኔ ቡድን የገዛ ካድሬዎቹን እና ባለስልጣናቱን**

**እያባረረ እና እያሰረ መሆኑ ታወቀ፤**

እድሜ ጠገቡ የወያኔ ስርዓት ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ የጤንነታቸው ሁኔታ ከምን ግዜውም በላይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ ተጠቆመ::

ፕሬዝዳንት ግርማ ባሳለፍነው ሳምንት ሰኞ ዕለት መስከረም 29 ቀን 2004 ዓ.ም የተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት መክፈቻ ስነ ስርዓት ላይ ንግግር ባደረጉበት ወቅት የጤንነታቸው ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑ ሊስተዋል መቻሉ ዘጋቢያችን ገልጸዋል::

እንደ ቤተ መንግስት ምንጮች ጥቆማ ከሆነ በአሁኑ ሰዓት የስልጣን ግዜያቸው ያለቀ ቢሆንም የወያኔ ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ በሀገር ውስጥ ስለሌለና የሚተካቸው ሁነኛ ሰው እስኪሾም ድረስ ባሉበት እንዲቀጥሉ የተደረገ መሆኑ ታውቋል::

መስከረም 29 ቀን 2004 ዓ.ም ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር በኢትዮጵያ ውስጥ በእሳቸው እድሜ ከፍተኛ የርሀብ አደጋ የተከሰተበት ዘመን ያሳለፍነው ዓመት መሆኑን በይፋ በመግለፃቸው የመለስ ውክልና ያለው በረከት ስምኦንን ጭምር አንጀት ያሳረረ እንደነበረም ታውቆዋል።

የወያኔ ቡድን በሀገሪቱ ርሀብ አልተከሰተም ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል የለጋሽ ድርጅት ሰራተኞች በቦታው በመገኘት በማረጋገጣቸው እውነታው የተጋለጠ ሲሆን በተለይ በቦረና እና በጎዴ የሰው ልጆች እና እንስሳት በየቦታው ወድቀው የቀሩበት ዘመን ያሳለፍነው ዓመት መሆኑን እድሜ ጠገቡ ፕሬዝዳንት ግርማ ማጋለጣቸው አንድም በህይወት የመቆየታቸው ሁኔታ ያለቀለት መሆኑን ተገንዝበው ሁለትም የስልጣን ዘመናቸው በማክተሙ የመጨረሻ ንግግሬ ይሆናል በሚል ያደረጉት ሳይሆን እንደማይቀር ተገምቶዋል።

በወያኔ ውስጥ ትርምስ እና ወከባ ተፈጥሮ እርስ በርስ እየታመሱ ባለበት በዚህ ግዜ ሰው ሳይዘጋጅ የእሳቸው ስልጣን መልቀቅ አደጋ ሊያስከትል ይችላል በሚል ስጋት በመቁረቢያቸው ግዜ በየአደባባዩ በዊልቸር እና በድጋፍ እያንገላቱዋቸው መሆኑ በገሃድ እየታየ ነው።

ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስን ይተካሉ ተብሎ ከሚጠበቁት መሀከል አንዱ አባዱላ ገመዳ ነው ቢባልም አሁን ባለው ሁኔታ ከመለስ ጋር ያለው ግንኙነት የሻከረ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል።

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በየቦታው የሚገኙ በለስልጣናቱን እያመሰ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይ የአይናቸው ቀለም አላመረኝም ብሎ ያላቸውን የብአዴንና የኦህዴድ ካድሬዎች ከቦታቸው እያነሳ ወደ ዘብጥያ እየከተተ መሆኑም እየተስተዋለ ይገኛል።

ማዕበል እንደሚያንገላታው መርከብ እዚያና እዚህ እየተወዛወዘ የሚገኘው አባዱላ ገመዳ ከዚህ ቀደም ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንትነት እና ከኦህዴድ ሊቀመንበርነት የተነሳውና የተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ሆኖ የተቀመጠ ሲሆን ሰሞኑንም ከኦህዴድ ስራ አስፈጻሚነት እንዲነሳ መደረጉ ታውቆዋል።

ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንትነት እና ከኦህዴድ ሊቀመንበርነት የተነሳው አባዱላ ገመዳ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ሆኖ የተቀመጠው ለመለስ ጥበቃ እና ቁጥጥር እንዲያመቸው ተብሎ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ አሁንም ከስራ አስፈጻሚነቱ አንስቶ በግርማ ወ/ጊዮርጊስ ቦታ ላይ ሊያስቀምጠው ይችላል ሲሉም ምንጮቹ ያላቸውን ግምት ጠቁመዋል።

ምንም እንኳዋን ከስራ አስፈጻሚነቱ ተነስቶ በፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ምትክ ሊሾም ይችላል እየተባለ ቢናፈስም መለስ ዜናዊ በአባዱላ ላይ ካለው ጥላቻ የተነሳ አሁንም ከሁሉም ስልጣን እያራቀ ባዶ ሊያደርገው አስቦ እንጂ ስልጣን ሊሰጠው እንዳልሆነም የሚገልፁ ወገኖች ብዙ ናቸው።

ዛሬ በወያኔ ቡድን ውስጥ እርስ በርስ መፈራረት እና መጠራጠር ነግሶ አንዱ አንዱን የጎሪጥ እያየ ያለበት ወቅት ከመሆኑም በላይ ሁሉም ለመለስ ዜናዊ ብቻ እንዲያጎበደዱ ለማድረግ ሆን ተብሎ የተሰራ ስልት እንደሆነም ምንጮቹ ይጠቁማሉ።

በአሁኑ ሰዓት የሀገሪቱን መሉ ስልጣን መለስ ዜናዊ ብቻ ጠቅልሎ ቢይዝም ከስር ሆነው የሚሰሩት በረከት ስምኦን..... ከትግራይ የመጣው ጻጋዬ በርሄ.... የደህንነቱ ጌታቸው እና ሌሎች ሁለት ወሳኝ ሰዎች ብቻ መሆኑን ያጋለጡት ውስጥ አዋቂ ምንጮች በካድሬዎቹ ውስጥ ውዥንብር እየነዙ በማስፈራራት ሰጥ ለጥ ብለው የታዘዙትን እንዲሰሩ ለማድረግ የተነደፈ ስልት መሆኑንም መንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለስልጣናቱን የመሻር እና የመሾም ተግባሩን አሁንም አስፋፍቶ እንደቀጠለበት ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡በዚህም መሰረት በኦህዴድ እና በብአዴን ባለስልጣናት ላይ የሚወሰደው እርምጃ ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፋ ከመሆኑም በተጨማሪም ወደ ዘብጥያ የሚወረወሩ ባለስልጣናትም ቁጥር እየጨመረ መምጣቱን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

በኦሮሚያ ክልል የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ የነበረችው ከስልጣንዋ ተባርራ በምትኩዋ ሌላ የተሾመ ሲሆን በአማራ ክልል የደብረ ብርሀን ከተማ ከንቲባዎችም ከስልጣናቸው መነሳታቸው ታውቆዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የስራ ብቃት የላትም ተብላ በግምገማ ተባርራ የነበረችው ሰዓዳ የተባለችው ካድሬ ተመልሳ ቦታውን የተቆጣጠረች ሲሆን አሁን ከስልጣንዋ የተባረረችው ወጣት ውጭ ሀገር ሳታስፈቅጂ ሄደሻል... ከነማ ጋር ግንኙነት አድርገሽ መጣሽ በሚል ተልካሻ ምክንያት ከስልጣንዋ ከማባረራቸውም በላይ ለጥያቄ ትፈለጊያለሽ በሚል ብዙ ግዜ ፖሊስ ጣቢያ እየተጠራች ሲያመላለሱዋት እንደነበርም የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል፡፡

ብአዴን በበኩሉ ከፍተኛና ዝቅተኛ ካድሬዎቹን በግምገማ ሰበብ አላላውስ ብሎ ወጥሮ ከመያዙም በላይ የተለያዩ ሰበቦችን እያከናነበ ለእስር እየዳረገ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት ውስጥ የደብረብርሀን ከተማ ሁለት ከንቲባዎች ወደ ዘብጥያ የወረዱ ሲሆን ሙስና ፈጽመዋል የሚል ታፔላ የተለጠፈባቸው መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ግለሰቦቹ ከህዝብ ጋር እጅግ የጠነከረ ግንኙነት ስላላቸው ብቻ በፍርቻ ሊከሰሱና ሊታሰሩ እንደቻሉ ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

አዲሱና ነባሩ ከንቲባ ከነካቢኔያቸው ሙሉ ለሙሉ ለእስር የተዳረጉ ሲሆን በነባሩ ከንቲባ ላይ የስድስት ዓመት እስራት ሲቀጣ አዲሱ ገና አዲስ ክስ ተመስርቶበት በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንደሚገኝም ከደብረብርሀን ከተማ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

ሰበቡ ሙስና ይሁን እንጂ ከተቃዋሚ አመራሮች ጋር በምስጢር ታይታችሁዋል.....ከህዝቡ ጋር እጅግ የጠበቀ ቁርኝት አላችሁ በሚሉና በሌሎችም ምክንያቶች እየተጠለፉ እየተባረሩና እየታሰሩ መገኘ ታቸው ወያኔ በገዛ ካድሬዎቹ ላይ እምነት እንደሌለው በግልፅ ያሳየ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ ገልጾዋል፡፡

በሌላ ዜና አባ ጳውሎስ ድንገት በቤተክህነት ግቢ ውስጥ በሚገኘው በመኖሪያ ቪላቸው ውስጥ እራሳቸውን ስተው ተገኙ ተብሎ ወደ አንድ የግል የህክምና ማዕከል ገብተው እንደነበር ከቤተክህነት ውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ገለፀ፡፡

የቤተ ክህነት ምንጮች እንዳሉት ከሆነ አባ ጳውሎስ በቅርቡ የሲኖዶሱ ጠቅላላ ጉባኤ የሚደረግበት እና ብዙ ጉዶች ሊጋለጡ የሚችሉበት ወቅት በመሆኑ ግዜውን ለማራዘምና የሚነሱ ጥያቄዎችን ለማዳፈን ሲባል ድንገት ታመሙ ተብሎ ወደ አንድ የግል የህክምና ማዕከል መወሰዳቸው ድራማ ነው ሲሉ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

እንደ ቤተክርስቲያንዋ ህግና ደንብ የእምነቱ አባት ያውም የመለኮሰ የተንጣለለ ቪላ እያለውና የራሱ መኖሪያ እያለው እዚያው ግቢ ውስጥ መሆን ሲገባቸው በአንዲት ሴት ግለሰብ ቤት ውስጥ በምስጢር ታመው ተኝተዋል መባሉ የሚያሳዝን እና የሚያሳፍር ከመሆኑም በላይ እምነቱን ጨርሶ መናቅ ነው ሲሉ ምንጮቹ በብስጭት ገልፀዋል::

ምን እንደሆኑና ምናቸውን እንደታመሙ በግልጽ ያልተነገረላቸው አባ ጳውሎስ በአሁኑ ግዜም በዚያው ሴትዮ ቤት ውስጥ ተኝተው የሚገኙ ሲሆን ለጳጳሳቱ ግን ገዳም ገብተዋል ተብለው እየተነገራቸው መሆኑን ምንጮቹ ጠቁመው በተለይ ብዙ ውስብስብ ችግሮች ተተብትባ ያለችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በየቀኑ የሚነሱና ውሳኔ ማግኘት የሚገባቸው ጉዳዮች እያሉዋት በምንቸገረኝ ስሜት ተነድተው በራቸውን ከርችመው በመውጣት ከገዳም ይልቅ የባልቲት ቤት ብሶባቸው...... ከፈጣሪ ይልቅ ግለሰቦችን እያመለኩ.....መገኘታቸው በእጅጉ የሚያሳዝን ና የሚያሳፈር ብቻ ሳይሆን መናቅ ነው ሲሉም ምንጮቹ አብራርተዋል::

በተለይ በአሁኑ ግዜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ውስጥ ከፍተኛ ትርምስ እና ጭቅጭቅ ባለበት ሰዓት...... በቅርቡ ደግሞ የሲኖዶሱ ጠቅላላ ጉባዔ የሚደረግበት ወቅት መሆኑን ተከትሎ አባ ጳውሎስ ድንገት ታመው ሴት ቤት ተኙ መባሉ አስገራሚ ብቻ ሳይሆን አስደማሚ ነው ሲሉም ምንጮቹ ገልፀዋል::

ገዳም ገብተዋል ጥቂት ቀናት ታገሱን በማለት ለጳጳሳቱ ቢነገራቸውም የመንፈስ አባታችን በመሆናቸው ያሉበት ገዳም እንድናያቸው ይነገረን ብለው ቢጠይቁም ያሉበትን ሊነግሩዋቸው ያልፈቀዱ ሲሆን ብዙዎቹ ጳጳሳት በሰውዬው ድርጊት ማዘናቸውን ተከትሎ በይፋ ቅሬታቸውን እየተናገሩ እንደሚገኙ ምንጮቹ ጠቁመዋል::

ከጥቂት ቀናት በሁዋላ ይደረጋል ተብሎ በሚጠበቀው የጠቅላላ የዓመታዊ የሲኖዶሱ ስብሰባ ላይ እጅግ ብዙ ጉዳዮች የሚነሱ መሆኑን ተከትሎ አባ ጳውሎስም ለሰሩት ጥፋት ምላሽ ስለሌላቸው ለግዜው ማምለጫ ዘዴ ብለው የፈጠሩዋት ይህችን ዘዴ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ዘንድሮ የራሴ ናቸው ያሉዋቸውን ጳጳሳት በሌሉበት ሊሾሙ በዝግጅት ላይ መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው አገልጠዋል::

በአሜሪካ ውስጥ ተመድበው የሚገኙት ጳጳሳትን አነስተው በሌሎች አዳዲስ የትግራይ ተወላጅ ሰዎች ለመተካት ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የጠቆሙት የቤተክህነት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይሄንና ሌሎች ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ሲሉ ታመምኩ ብለው በቤት ቤት ውስጥ መደበቃቸው አስገራሚ ነው ሲሉም ጳጳሳቱ እየተናገሩ ናቸው ሲሉ ምንጮቹ አብራርተዋል::

በአሁኑ ሰዓት ካሉት ጳጳሳት መሀከል ከጥቂቶቹ በስተቀር በአባ ጳውሎስ አመራር ያልተደሰቱ እና በድርጊታቸው የሚያዝኑ ብሎም የሚቃወሙ በመሆናቸው አባ ጳውሎስ አዳዲስ የትውልድ

ሀገራቸው ሰዎችን በመሾም ለራሳቸው ደጋፊዎችን ለማፍራት ሊሰሩ እንደሚችሉ ከወዲሁ እየተነገረ ይገኛል ያሉት ምንጮቹ በተለይ ከቀን ወደ ቀን በዙሪያቸው እየሰበሰቡዋቸው የሚገኙት ሰዎች የራሳቸው የትውልድ መንደር የሆኑትን ብቻ በመሆኑ ቤተ ክህነት የአንድ መንደር ሰዎች የተሰባበሰቡበት እየሆነ መምጣቱን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ከእምነት ይልቅ ፖለቲካ .....ከእውነት ይልቅ ክህደት......ከቤተክርስቲያን ይልቅ የግለሰብ ቤት ......ከፀሎት ይልቅ ስድብ......የሚበልጥባቸው አባ ጳውሎስ ታመሙ በሚል ሰበብ ከቤተክህነት ግቢ ደብዛቸው ጠፍቶ በግለሰብ ቤት ውስጥ ተኝተው መገኘታቸው የህዝበ ክርስቲያኑ ጥያቄ ከባድ እና ፈታኝ በመሆኑ ግራ ገብቶዋቸው የሚያደርጉት ሲጠፋቸው የወሰዱት የማታለያ ዘዴ እንደሆነም ያሳያል ያሉት ምንጮቹ ጠቅላላ ጉባዔው በተያዘለት ፕሮግራም የሚደረግ ከሆነ ከፍተኛ ጭቅጭቅና ንትርክ የሚጠብቃቸው መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የወያኔ ቡድን የአንድ ወገን የበላይነት እንዲነግስ እና ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን እንዲይዙ እያደረገ ባለበት በዚህ ግዜም የመከላከያ የሎቤድ ተሽከርካሪ ሹፌሮች የህወሀት አባሎች ብቻ እንዲሆኑ መደረጉ ተጋለጠ፡፡

ዛሬ ግሎባላይዜሽን እየተባለ የዓለም ህዝብ በአንድ መንደር እንሰባሰብ እያለ እየዘመረ ባለበት በዚህ ግዜ የወያኔ ቡድን ለአገዛዙ እንዲያመቸው ብቻ በጎጥ እየከፋፈለና እየበታተነ አንዱን ተጠቃሚ ሌላውን የበይ ተመልካች እያደረገ መገኘቱ የሚያሳዝን ተግባር ነው ያሉት አንዳንድ የመከላከያ አባሎች በተለይ በመከላከያ ውስጥ የሚደረገው አድልኦና ደባ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ብለዋል፡፡

ያልተማሩና በትግል ብቻ ግዜያቸውን ያሳለፉትን የበረሀ ታጋይ የነበሩትን የህወሀት ሰዎች የሻለቃ ማዕረግ ድረስ ሰጥተው ተራ አሽከርካሪ በማድረግ ያሰማሩዋቸው ሲሆን በአዲሱ መደባ ሙሉ ለሙሉ እነሱ ብቻ እንዲሆኑ መደረጉ ለሀገርም ለህዝብም የማይጠቅም ከመሆኑም በላይ አንዱ ተጠቃሚ ሌላው ተጎጂ ያስመስለዋል ሲሉም እነዚሁ የመከላከያ አባሎች ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በትግሉ ላይ ብዙ መስዋዕትነትን የከፈሉና ለውጤት ያበቁትን የህወሀት ታጋዮች አይናቸው ጠፍቶ ......እግራቸው ተቆርጦ....... እጃቸውን አጥተው...... መጦርና መደጎም ሲገባቸው እንደ አልባሌ እቃ በእርሻ ልማት ላይ ተሰማሩ ተብሎ ከከተማ አውጥተው ጭልጥ ያለ በረሀ ላይ የጣሉዋቸው መሆኑን የጠቆሙት እነዚሁ የመከላከያ አባሎች አሁንም ከፍተኛ የመኮንንነት ማዕረግ ሰጥተው የሎቤድ አሽከርካሪ ማድረጋቸው ሊጠቅሙዋቸው ሳይሆን ከአቅራቢያቸው ለማራቅ የተጠቀሙበት ስልት ነው ሲሉም የመከላከያ አባሎች በቁጭት ይናገራሉ፡፡

በመጨረሻም የኦሮሞ ነፃነት ግምባር (ኦነግ) ብሔራዊ ከውንስለ ከኦክቶበር 3-10 2011 ባከሄደው ጠቅላላ ስብሰባ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠልና ነፃነት ድረስ የሚለውን ነባር የኦነግ አቋም በድጋሚ ማፅደቁ ከተሰጠው መግለጫ ለማወቅ ተችሏል፡፡